# ደንብ

MONTGOMERY COUNTY
PUBLIC SCHOOLS

**ተዛማጅ ርእሶች፡-** COB-RA, JFA, JFA-RA, JHF, JHF-RA, JOA-RA
**የሚመለከተው ኃላፊ ጽ/ቤት፡-** ዋና የአካደሚ ኃላፊ
ዋና የሥራ ሀላፊ

## ወንበዴዎች፣ የወንበዴ እንቅስቃሴ፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ አውዳሚ ወይም ህገ-ወጥ የቡድን ስነ-ምግባርን መከላከል

I. **ዓላማ፡-**

የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ኣካደሚያዊ ግኝት እና ማህበራዊ እድገት የሚከናወኑት ተማሪዎችና ሰራተኞች ሰላም ሲሰማቸው መሆኑን ያምናል። ወንበዴዎች፣ የውንብድና እንቅስቃሴ፣ ወይም ተመሳሳይ አፍራሽ ወይም ህገ-ወጥ የቡድን ስነ-ምግባሮች (ከወንበዴ-ጋር-የተያያዙ ስነምግባሮች) በት/ቤቶች ሰላማዊ የሥራ እንቅስቃሴን ያደናቅፋሉ። የውንብድና አባል የሆኑ ተማሪዎች፣ ወይም በውንብድና እንቅስቃሴ ውስጥ የተካተቱ፣ ወይም በተመሳሳይ አፍራሽ ወይም ህገወጥ የቡድን እንቅስቃሴዎች የሚሳተፉ፣ ለእነዚህ እንቅስቃሴዎች የተጋለጡት ተማሪዎችን ጨምሮ፣ ለተለያዩ አሉታዊ የጤና ሁኔታዎች፣ ደህንነት፣ እና የትምህርት ውጤቶች አደጋ የተጋረጠባቸው ናቸው።

ስለዚህ፣ ለMCPS ተማሪዎች በውንብድና እንቅስቃሴ ውስጥ መሳተፍ በጥብቅ የተከለከለ ነው። ይህ ደንብ የመከላከል እርምጃን ተግባራዊ በማድረግ፣ አስቀድሞ ጣልቃ በመግባት፣ ፍቱን እንቅስቃሴዎችን፣ እና እንደአስፈላጊነቱ የተለዩ ውጤቶችን በሚመለከት፣ በት/ቤቶች ከውንብድና-ጋር-የተያያዙ ስነ-ምግባሮችን ለመከላከል ሂደቶችን ለመቋቋም መመሪያ ይሰጣል፣ እናም ከውንብድና-ጋር-የተያያዙ የተጠረጠሩ ስነ-ምግባሮችን በሚያሳውቁ/በሚጠቁሙ/በሚያጋልጡ ግለሰቦች ላይ አፀፋ ወይም ቂምበቀል እርምጃ እንዳይወሰድ ይከላከላል።

II. **መፍቻ፡-**

ሀ. *የወንበዴ ቡድን እንቅስቃሴ*—"ወንጀለኛ የወንበዴ እንቅስቃሴ" ማለት አዋቂ ቢፈፅማቸው ዋና ወንጀል የሚሆኑ የወጣት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የዋና ዋና ወንጀሎች ወይም ትግባሬዎችን የመፈፀም ሙከራ/ዎች፣ ወይም ለመፈፀም የሚደረግ ሴራ ማለት ነው።

1. በት/ቤት ተሽከርካሪዎች ወይም ንብረት ላይ ወይም በአጠገቡ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች። ኣንድ ሰው አንድን ግለሰብ፣ የአንድን ግለሰብ ጓደኛን ወይም የቤተሰብ አባል፣ በአካላዊ ሃይል ወይም በሁከት ለማስገደድ፣ ሊያግባባ ማስፈራራት ወይም ግለሰቡ በወንጀለኛ ወንበዴ ቡድን እንዲሳተፍ ወይም ለቆ እንዲሄድ፡-

   ሀ) በት/ቤት ተሽከርካሪ፤ ወይም
   ለ) በኤሌሜንታሪ ት/ቤት፣ በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ወይም የካውንቲ የትምህርት ቦርድ ንብረት በሆነ ቋሚ ንብረት ውስጥ፣ ወይም በ1,000 ጫማ ክልል ውስጥ የቀረበ እና ለኤሌመንታሪ ወይም ለሁለተኛ ደረጃ የትምህርት አግልግሎት የሚውል።

2. ተግባራዊነቱ-አነስተኛ ክፍል (ሀ) ከዚህ የሚከተሉት ይሁኑ አይሁኑ ተግባራዊ ይሆናል፡-

a) ወንጀሉ በሚፈፀምበት ወቅት ት/ቤቱ በስራ ላይ ነበር፤ ወይም

b) ወንጀሉ በሚፈፀምበት ወቅት ቋሚው ንብረት ከት/ቤት ዓላማዎች ውጭ ለሌሎች ዓላማዎች አገልግሎት ላይ ይውል ነበር።

ለ. *የወንበዴ ቡድኖች—"ወንጀለኛ ወንበዴ"* ማለት ሶስት ወይም ከዚያ በላይ ሰዎች ቡድን ወይም ማህበር የሆኑ ኣባሎች፡-

1. በግል ወይም በቡድን በወንጀለኛ እንቅስቃሴ መዋቅር ውስጥ የሚሳተፉ፤

2. ከተቀዳሚ ዓላማዎቻቸው ወይም እንቅስቃሴዎቻቸው የኣንድ ወይም ከዚያ በላይ ዋና ወንጀሎች፣ በኣዋቂዎች ቢደረጉ ዋና ወንጀል ተብለው የሚታሰቡ በወጣቶች የተከናወኑ ተግባሮችን ጨምሮ፤ እና

3. ኣንድ ከፍት ወይም ሚስጢራዊ ድርጅታዊ ወይም የትእዛዝ መዋቅር በጋራ ያላቸው።

ሐ. *የጣልቃገብነት እንቅስቃሴዎች* የግለሰብ ወይም የቡድን ኣቅርቦቶች በተወሰኑ ሁኔታዎች እና ጊዜ መጠን መጥፎ ስነ-ምግባሮችን ለማሻሻል/ለማረም የተመሰረቱ ናቸው።

መ. *የመከላከል እንቅስቃሴዎች* ከውንብድና ጋር የተዛመዱ ስነ-ምግባሮችን ብዛት፣ መነሻ ምክንያቶች፣ እና ውጤቶችን ግንዛቤ የሚሰጡ ት/ቤት-ኣቀፍ እንቅስቃሴዎች ናቸው። እናም የስነ-ምግባር ማሻሻል ድጋፎች እና የት/ቤት መሻሻል ጥረቶች የሁሉም የክፍል ደረጃዎች ኣካል ናቸው።

## III. ሂደቶች/ቅደም-ተከተሎች

ሀ. መከላከል፡-

ሁሉም ት/ቤቶች ከውንብድና-ጋር-የተያያዙ መጥፎ ስነ-ምግባሮችን መከላከልና የጣልቃ-ገብነት ስልቶችን እና/ወይም ሃላፊነት ያለው ማህበራዊ ስነ-ምግባርን የሚያስተምሩና የሚያጠናክሩ እንቅስቃሴዎችን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው። የሚከተሉትም ይካተታሉ፡-

1. የመከላከል ጣልቃ መግባት፣ እና ሙያን ማዳበር ጋር የተያያዘ የኣካባቢ ውሳኔ ኣሰጣጥ ለመምራት የት/ቤት ኣካባቢ ቅየሳዎች አተገባበርና ትንተና።

2. በመስፋፋት፣ ምክንያቶች/መነሻዎች፣ እና ከውንብድና-ጋር የተያያዙ ስነ-ምግባሮች፣ በማህበራዊ ክሂሎት እድገት፣ በኣወንታዊ የት/ቤት ኣካባቢ፣ በልዩነቶች መቻቻል፣ በዕድሜ-ተመጣጣኝ ያልሆነ የስነ-ምግባር ተጠባቂዎች፣ እና ከውንብድና-ጋር-የተያያዙ ስነምግባሮች ክውነቶችን በመከላከል ስልቶች ላይ የሚያተኩሩ ኣመታዊ ሙያን የማበልፀግ እንቅስቃሴዎች ለሁሉም ሰራተኞች።

3. በትምህርት ዓመቱ ውስጥ ለተቀጠሩ ሰራተኞች የሚሰጥ የሙያ ማዳበር።

4. ከአወንታዊ የስነ-ምግባር ድጋፎች ስርኣት፣ የጠባይ ትምህርት፣ ሁከት መከላከል፣ እና በሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የት/ቤት መሻሻል፤ እናም፣ እንደኣስፈላጊነቱ በኤሌመንታሪ ት/ቤት ደረጃ የሚተገበሩ ት/ቤት-አቀፍ መከላከያ ፕሮግራሞች።

ለ. ጣልቃ-መግባት፡-

1. ከውንብድና-ጋር-ስለተያያዙ ስነ-ምግባሮች መስፋፋት፣ የሚያመለክቱ መንስኤዎች፣ እና ውጤቶች፣ እና እንዳይደርሱ ለመከላከል ከቤተሰቦች እና የማህበረሰብ ባለጉዳዮች ጋር መተባበር።

2. ከውንብድና-ጋር-የተያያዙ ስነ-ምግባሮች ለሚያሳዩ ተማሪዎች ትምህርት፣ ምክር፣ እና ሌሎች ቀጥተኛ ጣልቃ-ገብነቶች። ጣልቃ-ገብነቶች፣ በነዚህ ሳይወሰኑ፣ የሚያካትቷቸው ለማረም ከቤተሰቦች እና የማህበረሰብ ባለጉዳዮች ጋር በመተባበር ፕላን ለማድረግ መፍትሔ ማቅረብ፤ በራስ-ለራስ-ጠበቃ መቆምና ራስን ማክበር ላይ ያተኮረ፣ የወደፊት መጥፎ ሁኔታዎችን የሚከላከል፣ እና ተጠቂዎችን ከቂምበቀል እና/ወይም በተጨማሪ ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ስነ-ምግባር ታሪኮች የሚጠብቅ የችሎታ ግንባታ።

3. የወንበዴ ቡድን፣ እና በሌሎች ተመሳሳይ አፍራሽ ወይም ህገወጥ የቡድን ስነ-ምግባሮች አባሎች የሆኑ ተማሪዎችን ማህበራዊ፣ ስሜታዊ፣ ስነ-ምግባራዊ፣ አካደሚያዊ ፍላጎቶችን በመመልከት ውጤታማ በመሆን የተረጋገጠላቸው የጣልቃ-ገብነቶች መስከ ዓላማ።

4. መረጃዎች ለሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ እና ለወላጆች/ሞግዚቶች ስለ ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ ጤና፣ እና የስነ-ምግባራዊ የጤና መገልገያዎች ከት/ቤት ጣልቃ-ገብነቶች ትግበራ በኋላ ከውንብድና-ጋር-በተያያዙ እንቅስቃሴዎች በመሳተፍ ለሚቀጥሉ ተማሪዎች። መረጃዎች በተጨማሪ ከወንበዴ-ጋር-በተያያዙ እንቅስቃሴዎች ተጠቂዎች ለሆኑ ወይም አእምሮአዊ፣ ወይም አካላዊ ጤንነት፣ ደህንነት፣ ወይም አካደሚያዊ አፈፃፀም ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የደረሰባቸው ቆሞ ተመለካች ለነበሩ ተማሪዎች መሰጠት አለባቸው።

5. አስቀድመው ከውንብድና-ጋር-የተያያዙ ስነ-ምግባሮች አወንታዊ ለውጦችን ላሳዩ ተማሪዎች፣ ከውንብድና-ጋር-የተያያዙ ስነ-ምግባሮች ተጠቂ ለነበሩ ተማሪዎች አእምሮ ማዛባትን/trauma የማስወገድ ስልቶች በመተግበር ላይ የሚገኙ፣ እና ተመልካች የነበሩና ከውንብድና-ጋር-የተያያዙ ስነምግባሮች ለወደፊት እንድያንሳርሩ ተግባራዊ ሚና ለወሰዱ ተማሪዎች እውቅና መስጠት።

ሐ. ተከታይ ውጤቶች፡-

ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ስነ-ምግባር ለተሳተፉ ግለሰቦች ወይም የሃሰት ክሶች ላቀረቡ ግለሰቦች ወቅታዊና ተገቢ ምርመራ ተካሂዶ እንደዚህ ዓይነት ኣምፅ መፈፀሙ ከተወሰነ በኋላ ተከታይ ውጤቶችና የመፈወሻ ተግባሮች ያለማቋረጥና በፍትሃዊነት መተግበር አለባቸው። ውጤቶች ከMCPS ደንብ JFA-RA፣ *የተማሪ መብቶችና ሃላፊነቶች*

## IV. የአመዝጋገብ ሂደቶች

ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ስነ-ምግባር ክውነቶችን ለማስታወቅ የሚከተሉት ሂደቶች አገልግሎት ላይ ይውላሉ፡-

ሀ. ሁሉም የት/ቤት ሰራተኞች ማንኛውንም የተጠረጠረ ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ስነ-ምግባር ክዋኔ ለርእሰመምህር ወይም ተወካይ ማስታወቅ አለባቸው። ሁሉም ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ስነ-ምግባር ዘገባዎች በፅሁፍ መሆን አለባቸው።

ለ. የMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ማቅረቢያ ቅጽ፣* በተማሪ፣ ወላጅ/አሳዳጊ፣ የቅርብ አዋቂ ዘመድ፣ ወይም የሰራተኛ አባል ሊሞላ ይችላል። አንዴ ከተሞላ በኋላ፣ ቅጹ ለት/ቤት ርእሰመምህር ገቢ ይደረጋል።

ሐ. አንድ ተማሪ ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ስነ-ምግባር ክውነት ለሰራተኛ አባል ሲያስታውቅ፣ የሰራተኛ አባሉ/ሏ ወድያውኑ ጣልቃ-በመግባት ምላሽ ያደርጋል/ታደርጋለች። የMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ* እንዲሞላ በመምከር፤ ክውነቱን ወድያውኑ ለት/ቤት

አስተዳዳሪ ያስታውቃል/ታስታውቃለች። ተማሪው/ዋ በነፃ ቅጹን መመዝገብ ካልቻለ/ች፣ የሰራተኛ አባል ተማሪው(ዋ)ን ቅጹን በመሙላት ያግዛል/ታግዛለች።

መ. በያንዳንዱ የትምህርት ኣመት መጀምርያ ላይ፣ ርእስመምራን ተማሪዎችን፣ ወላጆች/ሞግዚቶችን፣ እና የሰራተኛ አባሎችን ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ስነ-ምግባር ክውነቶች ዘገባ በMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ማቅረቢያ ቅጽ* ስለማቅረብ ያሳውቋቸዋል። እያንዳንዱ ት/ቤት የMCPS ፎርም 230-37 በት/ቤቱ ጽ/ቤት በኣማካሪ ጽ/ቤት፣ በሚድያ ማዕከል፣ እና በጤና ክፍል ይኖረዋል፣ እንዲሁም፣ ከተቻለ፣ በኣካባቢ ት/ቤት ድረ-ገጽ ላይ ፎርሙን መጫን።

V. **የምርመራ ሂደቶች/ቅደም-ተከተሎች**

ሀ. ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ስነ-ምግባር ሲፈፀም ከዚህ የሚከተሉት ቅደም-ተከተሎች ይካሄዳሉ፡ የMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ማቅረቢያ ቅጽ* እንደደረሰ፣ ርእሰመምህር ወይም ተወካይ፣ ረዳት ርሰመምህር፣ እና የት/ቤት የደህንነት መኮንን በ24 ሰዓት ውስጥ ምርመራ መጀመር ኣለበ(ባ)ት ዘገባው የእጅግ በጣም ኣሰቃቂ ደረጃ (የወንጀል እንቅስቃሴ፣ በማንዣበብ ላይ የሚገኝ አደጋ ወይም ረብሻ) ከሆነ ምርመራው ወድያውኑ 24 ሰዓት ሳይሞላ መጀመር ኣለበት። ከሁሉም ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ምርመራ ዘገባዎች የMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ማቅረቢያ* ኣገልግሎት ላይ ይውላል።

ዘገባው እጅግ በጣም ኣሰቃቂ ደረጃ (የወንጀል እንቅስቃሴ፣ በማዣበብ ላይ የሚገኝ አደጋ ወይም ረብሻ) ከሆነ በMCPS ደንብ COB-RA፣ *የከባድ ክውነት ዘገባ ኣቀራረብ* መሰረት፣ ኣግባብ ያላቸው የት/ቤት ስርኣት ፐርሶኔል እንዲያውቁት ይደረጋል።

ለ. የMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ማቅረቢያ ቅጽ* እና ኣባሪው የMCPS ቅጽ 230-38፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ምርመራ ፎርም*፣ በተማሪ ዘገባዎች ምስጢራዊነት መሰረት በት/ቤት ጽ/ቤት ውስጥ በሚስጢራዊ ማህደር ይያዛሉ። እናም ኣንድ ሚስጢራዊ ቅጂ ከት/ቤት ደህንነትና ፀጥታ መምርያ ጋር ይጋራል። እነዚህ ሰነዶች።

ሐ. የት/ቤቱ ርእሰመምህር እና/ወይም ተወካይ ከሁሉም ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ስነምግባር ውስጥ የሚፈረጁ ተማሪዎች ወላጆች/ሞግዚቶች ጋር ምርመራው ከተፈፀመ በ24 ሰዓት ውስጥ ይገናኛሉ።

መ. የት/ቤት ኣስተዳዳሪዎች እና/ወይም ተወካዮች ጣልቃ-ገብነቶች እና/ወይም ለክውነቱ ተገቢ የሆኑና ከስርዓትና ከት/ቤት ዲሲፕሊን ፕላኖችና ሂደቶች ጋር የሚስማሙ ተከታታይ ውጤቶችን ይተገብራሉ። ከወንበዴ-ጋር-በተያያዘ ስነ-ምግባር የሚሳተፍ ተማሪ ወይም ከወንበዴ-ጋር-የተያያዘ እንቅስቃሴ ምስክር የሆነ ተማሪ ብቀላ ወይም ኣፃፋ መውሰድ የተከለከለ መሆኑ እናም ከወንበዴ-ጋር-በተያያዘ ስነ-ምግባር ክውነቶች ከቀጠሉ ተጨማሪ የዲሲፕሊን እርምጃ እንደሚወሰድ ይነገረዋል።

ሠ. ከውንብድና-ጋር-በተያያዘ ስነ-ምግባር የተጠቃ ተማሪን እና ከውንብድና-ጋር-በተያያዘ ስነ-ምግባር የተሳተፈ ተማሪን የተሰየሙት የት/ቤት ሰራተኞች ጥቃቱ መቋረጡን ለማረጋገጥ በተካሄደው ምርመራ በሁለት ሳምንት ውስጥ የተለያዩ ስብሰባዎችች ያካሂዳሉ። እነዚህ ስብሰባዎች የምክር ጣልቃ-ገብነት ኣካል ሆነው ሊካሄዱ ይችላሉ። ከውንብድና-ጋር-በተያያዙ ስነ-ምግባሮች ተጠቅቶ ከነበረው ተማሪ ጋር ሌላ ተከታይ ስብሰባ ወይም ውይይት ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ስነ-ምግባር መቋረጡን ለማረጋገጥ ከተካሄደው ምርመራ አራት ሳምንቶች በኋላ ይካሄዳል።

ረ. የተወሰነ ከወንበዴ-ጋር-የተያያዘ ስነ-ምግባር በተጨማሪ በMCPS ደንብ COB-RA፣ *የከባድ ክውነት ዘገባ ኣቀራረብ* ላይ በተሰጠው ፍቺ መሰረት ከባድ ክውነቶች ተብለው ሊታሰቡ ይችላሉ። በነዚህ ጉዳዮች፣ በMCPS ደንብ COB-RA በተገለፁት ሂደቶች መሰረት በት/ቤት ኣስተዳዳሪ/ተወካይ ክትትል እንዲደረግባቸው ያስፈልጋል።

VI. **የመመዝገቢያ ፎርም መገኘት**

ሀ. የMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ማቅረቢያ ቅጽ፣* በMCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፤ እናም በሁሉም ት/ቤቶች ጽ/ቤት የአማካሪ ጽ/ቤት፣ በሚድያ ማእከል፣ እና በጤና ክፍል መገኘት አለበት።

ለ. የት/ቤት አስተዳዳሪዎች ሰራተኞችን ስለ የMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ማቅረቢያ ቅጽ፣* መኖር በየትምህርት አመቱ መጀመርያ ላይ ያስታውቋቸዋል፤ እናም በትምህርት አመቱ በሞላ በየወቅቱ ማሳሰብያ ይሰጧቸዋል።

ሐ. የት/ቤት አስተዳዳሪዎች ሰራተኞችን ስለ የMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ማቅረቢያ ቅጽ፣* መኖር በትምህርት የመጀመርያ ሳምንት ውስጥ፣ እናም በትምህርት አመቱ በሞላ በየወቅቱ በማሳሰቢያዎች ያስታውቋቸዋል።

መ. የት/ቤት አስተዳዳሪዎች ወላጆችን/አሳዳጊዎችን ስለ የMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ማቅረቢያ ቅጽ፣* እና የMCPS *ማህበረሰባዊ መገልገያዎች እና ወንበዴዎችን፣ የወንበዴ እንቅስቃሴ፣ ወይም ሌሎች ተመሳሳይ አፍራሽ ወይም ህገወጥ የቡድን ስነ-ምግባር የሚመለከቱ የኢንተርኔት ጣቢያዎች* ለተማሪዎችና ወላጅ/አሳዳጊዎቻቸው በተላከ በአመት-መጀምርያ መረጃ፣ በት/ቤት ዜና-መልእክት፣ የኢ-ሜይል ስራዓት እና በመጀመርያው የወላጅ-መምህር ህብረት እና የትምህርት ዓመት የት/ቤት ስብሰባ ያስታውቃሉ።

ሠ. አንድ ት/ቤት የተማሪ ወይም የወላጅ/ሞግዚት መጽሔት ካለው፣ ስለ የMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ማቅረቢያ ቅጽ፣* ስለመኖሩ መረጃ መካተት አእበት።

ረ. ተማሪዎች የMCPS ቅጽ 230-37፣ *ከውንብድና-ጋር-የተያያዘ ክውነት ዘገባ ማቅረቢያ ቅጹን* ለማንኛውም የሰራተኛ አባል (ለርእሰመምህር እንዲደርስ) መስጠት እንደሚችሉ ይነገራቸዋል። አንድ ተማሪ የዘገባ ቅጽ በግል ማቅረብ የማያስተማምነው ከሆነ ተማሪው የተሞላ ቅጽ ገቢ ለማድረግ እንዲችል አንድ አስተማማኝ ሳጥን በት/ቤቱ አስተዳዳሪዎች በተመረጠ/ጡ ቦታ/ዎች ሊቀመጥ ይችላል። አንድ ት/ቤት አስተማማኝ ሳጥን ካቋቋመ፣ ርእሰመምህሩ/ሯ ተማሪዎች፣ ወላጅ/አሳዳጊዎች፣ እና ሰራተኞች ስለ ቦታው እንዲያውቁ እና ሳጥኑ በያንዳንዱ የትምህርት ቀን መፈተሹን ማረጋገጥ አለበ(ባ)ት።

VII. **የድጋፍ አገልግሎቶች**

ከውንብድና-ጋር-በተያያዘ ስነ-ምግባር ተጠቂ ለሆነ/ች ተማሪ፣ እና ከውንብድና-ጋር-በተያያዘ እንቅስቃሴ የተሳተፉ ተማሪዎች፣ እና ቆሞ-ተመልካች ለነበሩ ተማሪዎች የሚከተሉት ድጋፎች አሉ።(ዝርዝሩ የተሟላ አይደለም)፣ እናም ውጤታማና ከትምህርት ቦርድ መመርያዎችና የMCPS ደንቦች ጋር የሚስማሙ ሌሎች አቅርቦቶችን ወይም የማህበረሰብ መገልገያዎችን ት/ቤቶች አይከለክሉም።

ሀ. የትምህርት ቤት/ስርዓት፡-

1. ትምህርት
2. የመማርያ ክፍል እና የአነስተኛ ቡድን ምክር አሰጣጥ
3. የትብብሮሽ ፕሮግራም አፈታት/የትምህርታዊ አስተዳደር ቡድን ሂደቶች
4. አወንታዊ የስነ-ምግባር ድጋፎች

5. ተግባራዊ የስነ-ምግባር ግምገማ/Functional Behavioral Assessment (FBA)

6. የስነ-ምግባራዊ ጣልቃ-ገብነት እቅድ/Behavioral Intervention Plan (BIP)

7. ሁለገብ የማህበራዊ ክህሎቶች ስልጠና

8. የጠባይ ትምህርት

9. ንዴትን የመቆጣጠር ስልጠና

10. የእውቅና ስነ-ምግባራዊ ምክር

11. የወላጅ/አሳዳጊ/ሞግዚት ተሳትፎ

12. የወላጅ/አሳዳጊ/ሞግዚት ስልጠና/ዎርክሾፖች

13. የእኩያ ድጋፍ ቡድኖች

14. የፕሮግራም ማሻሻያዎች

15. የት/ቤት ማሻሻያ እቅድ

ለ. ማህበረሰብ/ቤተሰብ፡-

*የመገልገያዎች ዝርዝር፣ የውንብድና መከላከያና ጣልቃ-ገብነትን የሚመለከቱ የማህበርሰብ መገልገያዎች እና የኢንተርኔት ጣቢያዎች* በት/ቤት ጽ/ቤቶች ይገኛሉ እናም በMCPS ድረ-ገጽ ይለጠፋሉ።

**VIII. የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ መገናኛ፡-MARYLAND STATE DEPARTMENT OF EDUCATION (MSDE)**

ዶር. ዴቦራ ኔልሰን፣
Deborah Nelson, Ph.D., NCSP
የክፍል ኃላፊ፣
የት/ቤት ደህንነት እና ሳይኮሎጂያዊ አገልግሎቶች
የተማሪ፣ ቤተሰብ፣ እና የት/ቤት ድጋፍ ክፍል
የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ
200 West Baltimore Street
Baltimore, MD 21201
ስልክ፡- 410-767-0294
ኢሜይል፡- Deborah.Nelson@maryland.gov

**ከዚህ ጋር የሚዛመዱ ምንጮች፡-** *የሜሪላንድ አኖቴትድ ኮድ* የትምህርት ኣንቀፅ፣ §7-424.2፤ የወንጀለኛ አዋጅ አንቀፆች፣ §9-801 እና §9-803፤ እና *የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት መምርያ፣ የሜሪላንድ ሞዴል መምርያ ወበዴዎችን፣ የወንበዴ እንቅስቃሴ፣ እና ተመሳሳይ አፍራሽ ወይም የህገወጥ ቡድን ስነ-ምግባር ለመቋቋም*

***የደንብ ታሪክ፡-*** ኣዲስ ደንብ ኦገስት 29፣ 2011፤ ሴፕተምበር 4፣ 2012 የተከለሰ፤ መለስተኛ ለውጦች ማርች 17፣ 2016፤ መለስተኛ ክለሳዎች ጁላይ 24፣ 2017።